በስደት ላይ ያለው ሕጋዊ ቅዱስ ሲኖዶስ
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የህዝብ ግንኙነት ጽ/ቤት

THE LEGITIMATE HOLY SYNOD OF THE
ETHIOPIAN ORTHODOX TEWAHEDO CHURCH
PUBLIC RELATIOIN OFFICE IN EXILE


ቀን: የካቲት 10/
Date: 02/17/1
ቁጥር: 001/20
Ref. No: 001/2

"በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።" ዮሐ3:16

# ብሔራዊ የመረጋጋትና የሰላም ጥሪ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ።

## ከሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሕዝብ ግንኙነት መምሪያ የተሰጠ ወቅታዊ መግለጫ

### "እጽናኑ፥ ሕዝቤን አጽናኑ ይላል አምላካችሁ።" (ኢሳ፥40: 1)

ለዘመናት ፍትህና ርትህ አጥቶ በምባገነኖች መዳፍ ስር የሚገኘው የኢትዮጵያ ህዝብ የሚያካሂደው መራራ ትግል ፍሬ አፍርቶ ዛሬ የሚታየው የለውጥ እንቅስቃሴ ከመቼውም ጊዜ በላይ ጠንከር ያለ ነው።

ለዚህ ለውጥ እንቅስቃሴ ዋና ምክንያት ለዘመናት የተንሰራፋው አምባገነናዊ ሥረዓት በተለይም የአሁኑ አገዛዝ የሕዝቡን መብት በማን አለብኝነት በመግፈፍ ተጠያቂነት የጎደለው አስተዳደርና በሙስና የተዘፈቀ አሰራር ማስፈኑ፣ ኢፍትሀዊነትና አድሎአዊነትን በሁሉም መስክ ማስፋፋቱ፣ መመርያው ያደረገው ዘረኝነትና ክፍፍል የህዝቡን አንድነትና የአገሪቱን ሉዐላዊነት አደጋ ላይ በመጣሉ፣ ያለፍርድ በማሰርና በመደብደብ ብሎም በመግደል የሕዝቡን ሰቆቃ በማብዛቱ ነው።

አገራችን ኢትዮጵያ ወደ ተሻለ ፍትሀዊ፣ ሕጋዊ፣ ዲሞክራሲያዊና ሰላማዊ የእድገት ጎዳና እንድትጓዝ ብዙ የጊዜ የገንዘብና የሕይወት መስዋዕትነት ተከፍሏል። ይሁን እንጂ በለውጥ ጊዜ የተደራጁ ኃይሎች በተደጋጋሚ ብቅ እያሉ የህዝቡን ድል በመንጠቅ አንባገነናዊና ከፋፋይ አስተዳደርን በመተካት፤ ለሕዝቡ የገቡትን ቃል ወደጎን በማድረግ፣ እንደገና ወደ ጨለማና አስከፊ ሥርዓት በመውሰድ ሀገሪቱንና ሕዝቧን ወደ በለጠ ውድቀትና የእርስ በርስ ግጭት ጥለዋል። አሁንም በመጣል ላይ ይገኛሉ።

ከዚህ ክፉ አደገኛ አዙሪት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለመውጣት አገሩን የሚወድ ዜጋ ሁሉ በአንድነት መታገል አለበት። የሕዝባችን ድምፅ መከበር ይገባዋል። ሕዝባችን የተነሳበትን እውነተኛ ነፃነት፣ እኩልነትና ሰላም የሰፈነባት ሀገር እንድትሆን የሚያደረገውን ትግል ከምንጊዜውም በተጠናከረ ሁኔታ መቀጠል ይኖርበታል። ታሪክ እንደሚያስተምረን አምባገነናዊ ሆኖ ሕዝብን በዘር፣ በሃይማኖት፣ በጎሣ ጥላቻና በፖለቲካ አመለካከት በመከፋፈል፣ በማጣላት፣ በመሳሪያ ኃይል ለረጅም ጊዜ መግዛት አይቻልም። በተለይም ዛሬ ዓለም በምትገኝበት የሥልጣኔ ደረጃ ይህ አይነት አሰራር ቀጣይነት የለውም።




80 TYCOS DRIVE TORONTO ONTARIO M6B 1V9 CANADA
ethiopianorthodoxchurchtoronto@gmail.com Tel. # 416-781-4802 fax # 416-781-0220

ስለሆነም ሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት ሀገሪቱ ወደ ከፋ የደም መፋሰስና ሽብር ውስጥ ከመግባቷ በፊት በአስቸኳይ፣

1. ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ የተጀመረውን መልካም እርምጃ በመቀጠል በግፍ የታሰሩ የፖለቲካና የሕሊና እስረኞችን በሙሉ መንግሥት እንዲፈታ።
2. በውስጥና በውጭ የሚገኙትን የሀገሪቷ የተቀዋሚ ፓርቲዎችን፣ ታዋቂ የሃገር ሽማግሎችን ሁሉ ያሳተፈ ሕጋዊነትና ተቀባይነት ያለው የሽግግር መንግሥት እንዲመሠረት።
3. አሁን የታወጀው የአስቸኳይ የጊዜ ዓዋጅ ሁኔታውን ወደ ተባባሰና አስከፊ ደረጃ የሚወስድ እንጂ መፍትሄ እንደማያመጣ መንግሥት በመገንዘብ እንዲያነሳው፡፡
4. የሕዝብ ሰላምና የሀገር መረጋጋት እንዲመጣ በሰው ሕይወት ላይ ምንም አይነት አደጋና ህልፈት እንዳይከሰት፣ በንብረት ላይ ጥፋትና ብክነት እንዳይደርስ በጋራ በመሆን፣ በወንድማማችነት፣ በአንድነት በመከባበር በሰላምና በውይይት የሁሉንም ዜጋ መብት ክብር ጥቅምና ሰላማዊ ኑሮን የሚያስከብር ሥራዓት እንዲፈጠር ሁሉም የበኩሉን አስተዋጽዖ እንዲያደርግ።
5. በጥብቅና በአጽንዖት ልናሳስብ የምንፈልገው ያለፉትን አስከፊ ድርጊቶች ወደ ኋላ በመተው ከጥላቻ፣ከበቀል፣ ከተንኮልና ከክፋት ነፃ በመሆን የወደፊት ሰላም ፍትህ የሰፈነባትን ሀገር እንድትመሠረት ሁሉም ኢትዮጵያዊ ኃላፊነቱን እንዲወስድ ቅዱስ ሲኖዶሱ ይማጸናል።
6. ሁሉም በያለበት ሆኖ ለሀገራችን ሰላም እድገትና ብልጽግና እንዲሠራ ጥሪያችንን እናቀርባለን።
7. ለፍትህ፣ ለነፃነት፣ ለእኩልነት፣ ለወንድማማችነትና ለእውነት የሚደረጉትን ትግሎች እየደገፍን የሃይማኖት አባቶች ፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ ምሁራን፣ የሀገር መከላከያ ሠራዊት አባላት፣ በኃላፊነት ቦታ የሚገኙ ዜጎች ሁሉ ከልብ የሆነና ያልተቆጠበ ጥረታቸውን ለሀገር ሰላም እንዲያደርጉ ጥሪ እናቀርባለን።

በስደት ላይ የሚገኘው ሕጋዊው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ አሁን የጀመርነውን ሱባኤ በመጽናት ሁሉም ለሀገሩና ለሕዝቡ የሰላም ባለቤት የሆነውን ልዑል እግዚአብሔርን እንዲማጸን በጥብቅ እናሳስባለን።

ወስብሃት ለእግዚአብሔር!

ሊቀ ካህናት ምሳሌ እንግዳ
በስደት ላይ የሚገኘው የሕጋዊው የኢ.ኦ.ተ.ቤክ ቅዱስ ሲኖዶስ
የሕዝብ ግንኙነት ክፍል ኃላፊ።

የካቲት 10 ቀን 2010 ዓ.ም.